# ሸብር - ከአፍጋኒስታን እስከ አዲስ አበባ

አብዱለከሪም

በኢትዮጲያ ወስጥ የጽንፈኛና አክራሪ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ መታየት የጀመረው ኢሕአዴግ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በሁዋላ አይደለም፡፡ የአክራሪ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ መታየት የጀመረው ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት በተለይም ከሳኡዲ አረቢያ የተንረንሰራፋው የዋሀቢ እስላም አክራሪዎች ጽንፈኛ እንቅስቃሴ ለስራ በሚል ሰበብ ከኢትዮጵያ ወደ ሳኡዲ አረቢያ በተለያየ ደረጃ ሲጉዋዙና ሲሰሩ የኖሩትን ኢትዮጵያወኖን በመሚለሚልና ወደ ሀገራቸው ተሚለሰው ይሄንኑ የዋሀቢ አክራሪ እስልምና እምነት እንዲስፋፋ ሚድረግ በጀሙበት ጊዜ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሚልኩ ከኩዌት፤ ከኳታርና ከየመን እንዲሁም ከአጎራባች ሱዳን ጭምር የአክራሪ እስልምና እምነት ተከታዮች ነባር የሆነውን የኢትዮጵያ እስልምና እምነት በሚጻረር አስርገው ባስገበዋቸወና በሚለሚሉዋቸው የዋሀቢና የሰለፊያ አክራሪ እስልምና እምነት ደቀ ሚዛሙቶቻቸው ወይንም ካድሬዎቻቸው ሁኔታውን የበለጠ ገፉበት፡፡

እነዚህ ወገኖች በደርግም ዘመን ተመሳሳይ አክራሪ እስልምናን ወደ ኢትዮጵያ ለሚስገባት የተለያዩ ሽፋኖችን በሚጠቀም ጥረት አድርገዋል፡፡ በተለይም በሐረር፣ በባሌ፣ በወሎና በሸዋ አካባቢ ሁኔታዎቹ እየገፉ ሜዳቸውን የተሚከተው ደርግ ችግሩን ለሚስታመም አልፈቀደም፡፡ የሂደቱ ቀንደኛ ሜዎችና አራሚጆች ናቸው ባላቸው ላይ ጠንካራ እርምጃ ወስዷል፡፡ በዚህ በተፈጠረው ከፍተኛ ሚናገጥና ሚሸበር ምክንያት እስከ ደርግ ወድቀት ድረስ የጎላ እንቅስቃሴ ሳይታይ ቆይቷል፡፡ ኢሕአዴግ ስልጣን በያዘበት ወቅት የነበሩትን የሚጀሚሪያዎችን ጥቂት አሚታት እንደ ሚልካም አጋጣሚ አድርጎ የወሰደና በኢትዮጵያ ወስጥ የዋሀቢና የሶለሪያን በእምነት ለሚስፋፋት ሲጥር የነበረው ሀይል በተለያዩ ሀገራት ለስራና ለትምህርት ሄደው የተሚሉሱ ወጣት ሙስሊሞችን አጥምዶ በሚስሚራት እንቅስቃሴውን በስፋት ቀጠለ፡፡ በዚህ ወቅት በዜግነቱ የሳኡዲና የየመን ተወላጅ የነበረውን የአልቃይዳ ሜሪ ቢላደን በሶሚሊያ ወስጥ 17 ቦታዎች ላይ የዋሀቢ እስልምና አክራሪ እምነት ተከታይ የሆነ የአልቃይዳና የአልኢትሀድ አል አስላሚያ አበላትን በዓለም አቀፍ ጂሀዲስቶች በሚታገዝ ወታደራዊ ስልጠና ይሰጥ ነበር፡፡ ከሶሚሊያ ወደ ኢትዮጵያ እየሰረጉ እንዲገቡ ለሚድረግም በተቻለው ሚጠን ሞክሯል፡፡

ከሳኡዲ፣ ከየመን፣ ከኳታር፣ ከኩዌት፣ ከግብጽ፣ ከሱዳንና ከሌሎችም አገሮች ተውጣጥቶ በአፍጋኒስታን ወታደራዊ ስልጠናና የፈንጂ ትምህርት የወሰደው የአልቃይዳ ዓለም አቀፍ አሸባሪ ሀይል አፍጋኒስታን ላይ ጦርነቱ መቁቁም ሲያቅተው እየተሰደደ በማምጣት የከተማው ሶሚሊያ እንዲሁም ሱዳን ነበር፡፡ ይህ ከሶሚሊያ የሚሳወና በተለያየ ሽፋን ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው አክራሪ እስላሚዊ ሀይል በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል ባሉት ቀጠናዎች የመግባትና የመውጣት እድሉን አግኝተዋል፡፡ ‹‹ከሀዋራጅያ›› የተባለው እስላሚዊ

አክራሪ ታጠቂ ሀይል የሱዳን ጠረፍን በማተረስ በቤንሻንጉል ጉምዝና አካባቢው ላይ ጽንፈኛ ሀይል አደራጅቶ በወታደራዊ እንቅስቃሴው ከባድ ጥፋት አድርሷል፡፡ ሰዎች ገድሏል፣ ንብረት አወድሟል፡፡ ይህ በጦር መሳሪያ በማታገዝ ወታደራዊ እንቅስቃሴ የጀመረው ሀይል ግንኙነቱ በአገር ወስጥ በጎረቤት አገሮች ካሉት አልሸባብና አልኢትሀድን ከመሳሰሉ ሀይሎች ጋር የዓላማ ትስስር ድጋፍ እያገኘ ያለ ሲሆን ጅምር እንቅስቃሴው የሚያሜሪው ልክ እንደ ናይጀሪያው ጽንፈኛ አክራሪ እስላሚዊ ሀይል <<ቦካ ሃራም>> እና በሚኢ እንዳለው <<አንሳር ዲን>> እንደሆነ ቅንጣት ልንጠራጠር አይገባም፡ በተለይም የአልቃይዳው መሬ የነበረው ኦሳማ ቢን ላደን የዋሀቢ አክራሪ እስልምና እምነት ተከታይ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ በኢትዮጵያ የዋሀቢ አክራሪ እስልምናን ለማስፋፋት የተደረገው ረዥም ጉዞና በቅርብ ዓመታ የተከሰቱት ድርጊቶች አሁን ያለወን ሁኔታ የግዴታ ቆም ብለን እንድናስብ ሀገራችንን ነቅተን እንድንጠበቅ ግድ ይለናል፡፡ ቢን ላደን ሶማሊያን ለቆ ከወጣ በኋላ የተወሰኑ ዓመታት የተቀማጠው ሱዳን ወስጥ ሲሆን እስላሚዊ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አቋቁሞ በዚህ ሽፋን የአልቃይዳ አባላትን ሲማለምልና ሲያሰለጥን የዋሀቢ እስልምና አክራሪ እምነትን ሲያጠምቅና ሲያስፋፉ ከቆየ በኋላ መጀመሪያ ወደ ነበረበት አፍጋኒስታን ተመለሰ፡፡ አፍጋኒስታን የሰለጠነው ተዋጊው የጅሀድ ዓለም አቀፍ አሸባሪና አክራሪ ሀይል በሶማሊያ ከገባ በኋላ በአልኢትሀድ አልኢስላሚያ አማካይነት ወደ ኦጋዴን ግዛት ገብቶ መንቀሳቀስ ጀምሮ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በቅንጅት እነ አብነግ (የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር) ከማንጠል ጥያቄው ውጭ በሸሪአ ህግ የሚመራና የሚተዳደር መንግስት የመመስረት ዓላማን ይዞ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ከአልቃይዳ ጋር ከተሰለፈው አልሸባብ ጋር ሳይቀር የትብብር፣ የመተጋገዝና ሚኒጃ የማለዋወጥ ትስስር ፈጡሩ፡፡

አፍጋኒታን ድረስ ሄደው በአልቃይዳ ከሰለጡኑት የተለያዩ አገራት ዜጎች ወስጥ ኢትዮጵያወያን የሉም አልነበሩም ብሎ መደምደም አይቻልም፡ ሶማሊያ ወስጥ አልሸባብና አልቃይዳ ሲያካሄዱት በነበረው የጅሀድ ጦርነትና ፀረ-ምዕራባወያን እንቅስቃሴ ከኦጋዴንና ከተለያየ የሀገራችን ክፍሎች በሜድ ስማቸወንና ማታወቂያቸወን ቀይረው አልተዋጉም ለማለት አይቻልም፡ እዚህ ሁሉ ተደጋጋሚ በሽፋን ሲሰሩና ሲካሄዱ በቆዩ የዋሀቢና የሶሪያ አክራሪ ሙስሊሞች የሽፋን እንቅስቃሴ ገሀድ የወጣው የኢትዮጵያ እስልምና ጠ/ምክር ቤት አሜራርን በዋሀቢ እስላሚዊ አክራሪዎች ቁጥጥር ስር በማድረግ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን በዋሀቢ እምነት ስር ለማከለፍ እንዲችሉ የሞት የሽረት ትግል አድርገዋል፡፡ በቅርቡ እካደረጉት ቀደም ሲል አስቀድሞ በ1987 - 88 አካባቢ በዚሁ በሞርካቶው መስጊድ አካባቢ ተነስቶ የነበረው ብጥብጥ በኋላም ወደ ግጭት ያመራወና የሰው ሞትና የንብረት ወድመት ያስከተለወም ዋነኛ ታሪክ የእስልምና ጉዳይ ጠ/ምክር ቤትን አሜራር እኛ መቆጣጠር አለብን የሚሉ ወገኖች በስልጣን ላይ ከነበረው ክፍል ጋር በመስናና በመሳሰለው ሲወነጃጀሉ ቆይተው በአዲስ አበባ ሕዝበ ሙስሊሙም ሰልፍ እንዲወጣ ተደርጎ መንግስትም ለማሸምገልና ለማደራደር ችግሩንም ለመፍታት ያደረገው ጥረት በከፍተኛ የመንግስት ጥረት ከሽፈ፡፡ ልክ አሁን እንደያዙት ዓይነት መሻሻው የአስተዳደራዊና የመስና ጥያቄ የነበረ ሲሆን በዚህ ሽፋን ስር የነበረው ሩቅ ዓላማ ግን አሜራሩን በመቆጣጠር ዋሀቢዝምን ማስፋፋት በሂደትም ሀገሪቷን

በሀይል እስላሚዊ ሀገር አድርጎ የመቀየርና በኋላም በሻሪዓ የሚተዳደር እስላሚዊ መንግስት መመስረት የሚለው ነበር፡፡ ይህንን እውነት በከተማውና በገጠሩ የሚኖ የችግሩ ተጎጂዎች የሆኑ ሙስሊም ወንድሞችና እህቶች በገሀድ መስክረዋል፡፡ ከእነሱም ምስክርነት ሌላ ተጨባጭ የሆነው ማስረጃ ሳኡዲ አረቢያ ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ የዋሀቢ አክራሪ እስልምና ሚኒ በግልጽ ከነፎቶው የጠራ አማርኛ እየተናገሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን <<ለጀሀዳዊ ሀረካት>> ሲቀሰቀስ ፣ ኢትዮጵያውያን አክራሪ ሙስሊሞች ለጅሀድ ጦርነት ወታደራዊ ዝግጅትና ስልጠና ሲያደርጉ የሚያሳይ ፊልም ተቀርጾ የመጣውና ቀደም ሲል በስዉር የተሰራጨው ሲዲ አሁን በገሀድ አሁን በገሃድ ቀርቦልን ልናየው ችለናል፡፡ ይህ ደግሞ በቂና ከበቂ በላይ ማስረጃ ነው፡፡ በዚህ ወስጥ የዋሀቢው አክራሪ እስልምና ሚኒ ኢትዮጵያን የካፊሮች አገር ማን አደረጋት ጠንትም የእኛው ነች ከተፈለገም ወደፊት በሂደት ስሟን እንቀይራለን ሲልም ይደመጣል፡፡ሙስሊሙን ለጅሀድ እንዲነሳም ቀስቅሷል፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ የሙስሊሙም፣ የክርስቲያኑም፣ የካቶሊኩም፣ የፕሮቴስታንቱም፣ የዋቄ ፈታ እምነት ተከታዩም፣ የኢ-አማኞችም አገር ነች፡፡ ሁሉም እኩል መብትና ነጻነት አላቸው፡፡ አሁን ያለው መንግስትም ከሀይማኖት ገለልተኛ የሆነ ነጻ (Secular) መንግስት ነው፡፡ ነገር ግን የሌሎችን የተለያዩ ሀይማኖቶች ነጻነትና መብት ረግጦና ደፍቆ በሀይልም አጥፍቶ በሸሪአ ሕግ የሚተዳደር እስላሚዊ መንግስት እንመሰርታለን ብሎ ማለብ በእጅጉ አስቸጋሪ ነው፡፡

በቀድሞው የግብጹ ፕሬዝዳንት ሆስኒ ሙባረክ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ለመካፈል አዲስ አበባ ሲመጡ ተሸሎክሉከው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመግባትና አ/አበባ ወስጥ ቤትና መኪና በመከራየትና መሳሪያም በማዘጋጀት የግድያ ሙከራ ያደረጉ የአልቃይዳ አባላት መሆናቸውን ማጠራጠር አይገባም፡፡

በሃገራችን እየሰማን ያለነው፣ የጽንፈኛው አክራሪ ሙስሊም የዋሀቢም ሆነ የሰለፊያም እንቅስቃሴ፣ "የለም የመስጊዱ ጥያቄና አቤቱታ ምርጫውን በመቃወምና የሀይማኖት ነጻነታችን ይከበር" በሚል ካባ ሽፋን የሚካሄድ ነው፡ መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገብቱዋል ተወካዮቻችን ታስረዋል ይፈቱ <<ጂሀዳዊ ሀረካት>> የሚለው ፊልም የታሰሩትን ሙስሊሞች ለመወንጀል ሲባል መንግስት ያቀነባበረው የፖለቲካ ስራ ነው፡፡ የሚሉት ከእውነታው እጅግ ያፈነገጡ የክህደትና የሸፍጥ አባባሎች ሌላውን ሕብረተሰብ ለማሳሳት የሚዘ ተራ ፕሮፖጋንዳዎች ናቸው፡፡ ድሮስ "አዎን እኛ እአክራሪ ሙስሊሞች ነን፣ በሸሪያ የሚተዳደር እስላሚዊ መንግስት ለመመስረት እንፈልጋለን፡፡" እንዲሉ ማጠበቀ ጅልነት ነው የሚሆነው፡፡ "መጅሊሲ ያካሄደው ምርጫ አግባብ አይደለም መውረድ አለበት" የሚለው ሕግን ያልተከተለ ለዓመታት የዘለቀው ጩኸት በግልጽ የሚያሳየው ዋሀቢ አክራሪ ሙስሊሞች እያሉት ያሉት "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ምክር ቤት አመራርን በግድ እኛ መቆጣጠር አለብን፣ ይህ ካልሆነ ጩኸታችን አይቆምም፣ አይገታም" ነው፡፡ አመራር ላይ የተቀመጡትን የሚጠወስ አብዛኛው ሙስሊም ምን ይበል? እነሱም ወጥተው ይቃወሙ? ሌላ ድብቅ ዓላማ ስዉር ደባ ከጀርባ ባይኖር ኖሮ "እስኪ እነዚህ አዲስ የተሚጡትን ደግሞ ግዜ ሰጥተን እንያቸው፣ ለውጥ ያመጡ ወይንስ አይመጡም" ማለትም ማለትም ባልገደደ ነበር፡፡

ዋሃቢዎችና ሐላፊዎች ይሄንን ማስማትም ማየትም አይፈልጉም። ዛሬ በየሳምንቱ አርብ ወጣቱን ማስለም ለማስተባበር (እንደወም ባለፈው አርብ ከጁማአ ስግደት በኋላ የነበረው ተቋወሞ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያስተላለፈወንና እውነቱን የቃጋለጠወን <<ጅሃዳዊ ሀረካት>> ፊልም በመቃወም ነበር) ወደ አመጽ ለመግፋት እየተደረገ ያለው ጥረት ሌላው የዚህ **የጽንፈ ነት** አብዩ አካል ነው፡፡

እዚህ ላይ እነዚህ ወገኖች ያልተረዱት አንድ አብይ ቁም ነገር ቢኖር ሀይማኖታዊ ነጻነታቸው መብታቸው በተከበረባት ኢትዮጵያ የሌላወም ማስለም ያልሆነ ዜጋ መብትና ነጻነቱ እምነቱም ጭምር የተከበረ መሆኑን ነው፡፡

በእርግጥ ዛሬም በተለያየ ሽፋንና ዘዴ ከተለያዩ አረብ ሀገራትና ከወኪሎቻቸው መንግስታዊ ባልሆኑ እስላማዊ የግብረ ሰናይ ድርጅቶች አማካይነት (በኤምባሲም ይሁን በግለሰብ ነጋዴዎች) የሚፈልጉት ብቻ ሳይሆን ዓላማቸወን ለማስካት እንዲችሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ መሆኑን ማጠራጠር አይቻልም። እዚህ ላይ አንድ ሰው በጥቂት ጊዜያት ወይንም ዓመታት ወስጥ በሀብትና በገንዘብ መጥቆ ሲወጣ እንዴት ነው? ምንጩ ከየት ነው? ብሎ ማጠየቅ ለሕዝብና ለሀገር ደህንነት ሲባል ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

በአሁኑ ሰአት የአረቡን ዓለም አብዮት ተከትሎ በየሀገራቱ የተፈጠረው ትርምስና ምስቅልቅል ከማንም በላይ የበጀወና የተመቸው ለአልቃይዳ ነው፡፡ የአሜሪካና የስለላ ድርጅትና ሌሎችም በቅርቡ ባካሄዱትና ይፋ በሆነ ጥናት አልቃይዳ ከቢላደን ሞት በኋላ ተጠናክሮ ቀጠለ እንጂ አልከሰመም። በየሀገራቱ ባሉ የተለያዩ ግጭቶች የጦር መሳሪያ እንደልቡ ማግኘትና ማስታጠቅ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ትጥቅ ያለው ወታደራዊ ሀይል እስከ ሚደራጅትና ወኒያ እስከመካፈትና ቦታዎችንም እስከ መቆጣጥር ተራምሟል፡፡ በቅርቡ በማሊ ቲምቡክቱን እስከ መቆጣጥር የደረሰው የአልቃይዳ አጋር የሆነው አክራሪ የመስለም ታጣቂ ሀይል (ኢንሳር ዲን) በፈረንሳይ ወታደሮች ድጋፍ ለቆ የወጣ ቢሆንም ሁንም ቦታ ይዞ እየተዋጋ ይገኛል፡፡ የናይጀሪያው ቦኮ ሀራምም እስላማዊ አክራሪ ታጣቂ ሀይል ሲሆን ክርስቲያኖችንም ሆነ ምዕራባወያንን ማለትም ከእነሱ ውጭ ያለን ሰው እስከ መግደል ድረስ የሄደ ነው፡፡

በእኛም ሀገር የተከሰተው <<ካሚጅያ>> እስላማዊ አክራሪ ታጣቂ ቡድን በአጭሩ ባይገታ እርምጃው ወደየት ነበር? በቅርቡ ከሚሴ ላይ የተከሰተው (መሳሪያ ታጥቆ ፖሊስ ጣቢዩ መዝረፍ፣ ፖሊስ መግደል፣ ኤሌክትሪክ ማስመር ማብጣጠስ፣ በመጂሊስ ምርጫ የተሳተፉትን ለይቶ ሚደብደብ ወዘተ) ይሄስ ወደየት ነው የሚያመራው፡፡

ይህ እጅግ አደገኛ የሆኑ የእስልምና አክራሪ ሀይሎች እንቅስቃሴ በተጨባጭ በሚታይበት ሁኔታ – – – የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ይህ ችግር የለም ጥያቄው የመብት ጥያቄ ነው ከሚል

በሀገር ወስጥና በውጭ በተለያዩ ማናኛ ብዙሀንና በድረገጻቸው የሚያሰሙት ድምጽ ተረባርበን ኢሕአዴን እንጣል ከሚለው ጫፍን ጥላቻቸው በማሳሳት ሲሆን እውነታው ይጠፉቸዋል ለማለት አይቻልም፡፡

ማንግስት ይህንን በመብት ሽፋንና ስም እየተጠለለ አደገኛ እስላማዊ አክራሪ የፖለቲካ አጀንዳ ይዞ የሚንቀሳቀሰወን ቡድንና ያሰለፈወን ሀይል በማከታተል ሕዝቡንም ሀገሪቷንም ሰላሟና ደህንነቷን የማጠበቅ ከአደጋም የማካላከል ሃላፊነቱን የመወጣት ግዴታ አለበት፡፡

እስላማዊ አክራሪነትም ሆነ የትኛወም ዓይነት ሀይማኖታዊ ጽንፈኝነት ለሀገር ልማት እድገት ሰላም አይበጅም፡፡ የእርሰ በእርስ ግጭትም በማስከተል ለብሔራዊ ሰላምና ደህንነት አደጋ ሊሆንም ይችላል፡፡ በማሆኑም ከወዲሁም በአስቸኩዋይ ሊገታ ይገባል፡፡

በሌላ ጎኑ በርካታ ኢትዮጵያወን ወጣት ሙስሊሞችን ስኮላርሽፕ በማስጠት በሱዳን፣ ሳኡዲና የመን የአክራሪዎች ተቋም ገብተው እንዲማሩ ወደ ሀገራቸወም ተመልሰው ይሄንኑ እምነት በዝግታና በዝምታ እንዲያስፋፉ ተደርጓል፡፡ ዓለም አቀፍ ጂሀድ ዋና መናሃሪያው ማስባሰቢያው አፍጋኒስታን ስለነበረችና ቢንላዲንም እዛው ይገኝ ስለነበር ኢትዮጵያወንና ወጣት ሙስሊሞች ለስራ ከሄዱባቸው የተለያዩ አረብ ሀገራት (ሳኡዲ አረቢያ፣ የመን ሱዳን ከመሳሰሉት አገሮች ዜግነታቸወን እየቀየሩ ወደ አፍጋኒስታን የሄዱ እንደሚኖሩ ይታመናል፡፡ ኢሕአዴግ ስልጣን በያዘበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ኢትዮጵያ ወስጥ ገብተወና ተመዝግበው ሲንቀሳቀሱ ከነበሩት እስላማዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወስጥ አፍጋኒስታን ውጊያ ላይ በነበሩ ሙጅሀዲኖች የሚመሩ ነበሩ፡፡ በወቅቱ ለነበረው የእልስምና ጉዳዮች ጠ/ምክር ቤትን ለመቆጣጠርና አሚራሩን ለማውረድ የተፈጠረው አለመግባባት እየተካረረ እንዲሄድና በኋላም ረብሻና ሁካታ እንዲፈጠር በተደረገው እንቅስቃሴሰ ወስጥ እነዚህ ወገኖች እጃቸው የነበረበት ማሆኑ ስለተደረሰበት ከአገር እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

በተለይ በአሁኑ ወቅት የአልቃይዳን ሚብ በአፍሪካ ዳር እስከ ዳር ለማዝርጋት በተያያዙት እንቅስቃሴ በየሀገራቱ ወስጥ ሕዝቡ በተለያየ ሁኔታ በኑሮ ወድነትና በስራ አጥነት በማሳሰለው እንዲያምጽና ከቁጥጥር ውጭ እንዲወጣ መንግስትንም እንዲበጠበጥ እንዲናጋ የሚድረጉን ስልት አልቃይዳ ከማረጃው ጀርባ ሆኖ ግፊት በሚድረግ እየተጠቀማበት ነው፡፡ አልፎ አልፎ የተሳካ ወጤትም አግኝቶበታል፡፡ ሊቢያ፣ ግብጽ፣ ሶሪያና የመን ተጨባጭ ማስያ ሲሆኑ ማሊንም መውሰድ ይቻላል፡፡ እነዚህ የጽንፈኛ አክራሪ ሙስሊም እምነት አራማጆች በእምነቱ ወስጥ የተለያየ ስም ቢኖራቸወም ግባቸው አንድ ነው፡፡ በሸሪዓ ሕግ የሚመራ እስላማዊ መንግስት እንዲፈጠር ሚድረግ የሌላወን እምነት ተከታይ መብት ሚገጥና ማጥፋት፡፡ ይህ ደግሞ መቼም የትም ኢትዮጵያ ወስጥ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡